# የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 959/2015

Government Employees' Pension Proclamation No. 1267/2014 Implementation Directive No. 959/2015


የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር
Public Servants' Social Security Administration

ህዳር 30፣ 2015

# ማ ው ጫ

ገጽ


መግቢያ ………………………………………………………...………………2

ክፍል 1 ጠቅላላ……………………………………………………….….…......3

ክፍል 2 ስለ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ምዝገባና ማስረጃ አደረጃጀት……………………………………………..…..….4

ክፍል 3 ስለጡረታ ዐቅድ ፈንዶችና መዋጮዎች …………………………..6

ክፍል 4 የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች….…8

ክፍል 5 የልደት ዘመን አያያዝ ……………………………….…….16

ክፍል 6 የአገልግሎት ዘመን አያያዝ ……………………….…………19

ክፍል 7 ለጡረታ አበል አወሳሰን ስለሚያዝ ደመወዝ ……………20

ክፍል 8 የጡረታ አበል ውሣኔና ክፍያ አፈጻጸም …………….…….21

ክፍል 9 በወኪል አማካኝነት የጡረታ አበል ስለመክፈል …………23

ክፍል 10 ስለጡረታ አበል ውሳኔ መነሻ ጊዜና ውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰን ………………………………………….…........26

ክፍል11 በጡረታ መብትና ጥቅም ላይ ስለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሳኔ አሰጣጥ …………………………………………..……….29

ክፍል12 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች …………………..….30

# ***<u>መግቢያ</u>***

*የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ለጡረታ ባለመብቶች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስልት መቀየስ አስፈላጊ በመሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶችን እና ሠራተኞችን የምዝገባ ማስረጃ አደራጅቶ በመያዝ፣ ዘመናዊ የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ስርአት እንዲዘረጋ ፣ የጡረታ አበል ውሳኔ ሥራ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈፀም ለማድረግ፣ እና የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማስረጃዎችን ለፈጻሚው ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት የወጡ መመሪያዎችን ማጠቃለል እና ከመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 ጋር በማገናዘብ ማስተካከል ስለሚገባ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 61/2/ ለአስተዳደሩ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለው የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ወጥቷል፡፡*

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 959/2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

ሀ. በመንግስት የሚካሄድ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ማለት የማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣የመሰረተ ልማትና መሰል ጉዳዮችን ለማስፈጸም ለተወሰነ ጊዜ የሚቋቋሙና የሚዘረጉ መንግስታዊ ሥራዎች ሲሆኑ በውጪ መንግሥታት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተራድኦ (ድጋፍ) የሚካሄዱትን መንግሥታዊ የልማት ወይም የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

ለ. ማስረጃ ማለት ለምዝገባ፣ ለጡረታ አበል ውሳኔ ወይም ክፍያ ለመፈፀምና የጡረታ ባለመብቱን ማንነት ለማረጋገጥ ወይም መረጃን ወቅታዊ ለማድረግ በአሠሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚቀርብ የመንግሥት ሠራተኛው ወይም የጡረታ ባለመብቱ የግል፣ የአገልግሎት፣የልደት ዘመን፣ የቤተሰብ፣ የደመወዝና ሌሎች አግባብ ያለቸው የጽሁፍ መረጃዎች ናቸው፡፡

ሐ. በሌላ ምክንያት ከሥራ መሰናበት ማለት ሠራተኛው በሚሰራበት መሥሪያ ቤት ሥራና ተያያዥ በሆኑ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ምክንያት ሳይሆን ለአሠሪው ሳያሳውቅ ከሥራ በመቅረት፣ ከሥራው ጋር ባልተያያዘ ጥፋት ምክንያት በመታሰር፣በቅነሳ ፣መሰወር፣ በችሎታ ማነስና በሌሎች መሰል ጉዳዮች ምክንያት ሥራ የሚለቅ ወይም የሚተው ሠራተኛን የሚመለከት ነው፡፡

መ. የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት (e-service) ማለት አሠሪ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞቻቸውን የጡረታ ቅፅ 1 ምዝገባ

አደራጅተው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለአስተዳደሩ ሲልኩ የማስረጃ ማጣራት፣ ምዝገባ እና የጡረታ መለያ ቁጥር የማሳወቁ ሂደት ሙሉ በሙሉ በቀጥታ (on line) የሚካሄድበት የአሰራር ስርአት ነው፡፡

ሠ. አዋጅ ማለት የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 ነው

ረ. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ አንቀጽ (2) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ምዝገባና ማስረጃ አደረጃጀት

### 3. ስለ ምዝገባ

1. በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የሚሸፈኑ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችና የመንግሥት ሠራተኞች መመዝገብ አለባቸው፡፡
2. ተመዝግበው የጡረታ መለያ ቁጥር እንዲሰጣቸው ለተደረጉ የመንግሥት ሠራተኞች የዐቅድ አባልነታቸውን የሚያረጋግጥ የዐቅድ አባልነት ካርድ ይሰጣቸዋል ወይም በኢ-ሰርቪስ (e-service) አገልግሎት የጡረታ መለያ ቁጥራቸውን እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ ክፍል በዝርዝር በተገለጸው መሠረት በ60 ቀናት ውስጥ ወይም የጡረታ አበል ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የማስረጃ ለውጥ ለማያቀርብ የመንግሥት ሠራተኛ፣ ባለመብት ወይም ተተኪዎች የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በአስተዳደሩ ተደራጅቶ በተያዘው ማስረጃ መሠረት ነው፡፡

### 4. ለምዝገባ ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች

1. የአስተዳደሩ የምዝገባ ባለሙያ ከአሠሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቅጽ ጡ.1 ተሞልቶ ሲቀርብለት የሚከተሉትን ማስረጃዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ. የሥራ መጠየቂያ / የሕይወት ታሪክ ፎረም

ለ. የቅጥር ደብዳቤ /የኮንትራት ውል፣

ሐ. ጋብቻ ተፈጽሞ ከሆነ ጋብቻን ለመመዝገብ ሥልጣን ካለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፤

መ. ፍቺ ተፈጽሞ ከሆነ ፍቺ ስመፈጸሙ ስልጣን ካለው አካል የተሰጠ ማስረጃ፣

ሠ. . ዕድሚያቸው 18 ዓመት ያልሞላ ልጆች፤ (አካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው 21 ዓመት ያልሞላ) ልጅ ካለ ስልጣን ካለው አካል የተሰጠ የልደት ሰርተፍኬት፡-

ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

2. ከላይ የተገለፁት ማስረጃዎች ሲረጋገጡ ስርዝ ድልዝ የሌላቸው መሆኑን እና የተለያየ የልደት ዘመን አለመሞላቱን አረጋግጦ ይረከባል፡፡ ይህ ሳይሆን ከቀረ እንዲስተካከል ተመላሽ ያደርጋል::

3. የማስረጃ ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ፍቺ ተቀባይነት የሚኖረው ፍቺው በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ሲቀርብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ከተፋቱ በኋላ የሚፈፀምን ጋብቻ ለማረጋገጥ የሚቀርበው ማስረጃ ተቀባይነት የሚኖረው ዋና ባለመብቱ በህይወት እያለ ዳግም የተጋቡ ስለመሆኑ እና አብረው ሲኖሩ እንደነበር ከወሳኝ ኩነት ተረጋግጦ የቀረበ ማስረጃ ወይም በሽምግልና እርቅ የፈጸሙበት ሰነድ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ማስረጃው ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

## 5. <u>ስለ ማስረጃዎች አደረጃጀት</u>

1. በአስተዳደሩ ተደራጅተው የሚያዙት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱና የመንግሥት ሠራተኛው ማስረጃዎች በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 3 እና 4 የተመለከቱት ናቸው፡፡
2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞቻቸውን የግል ሁኔታ፣ የአገልግሎት ፣የቅጥር ፣የዝውውር፣የስንብት ወ.ዘ.ተ የቤተሰብ ማስረጃዎችን አደራጅቶ የመያዝና ይህንኑ በአዋጁ አንቀፅ 6 መሠረት በ60 ቀናት ውስጥ አስተዳደሩ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተደራጅተው መያዝ ያለባቸውን የመንግሥት ሠራተኞች ማስረጃዎች በአሠሪው የመንግሥት መስሪያ ቤት በመገኘት የአስተዳደሩ ባለሙያዎች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ማህደር ምርመራ ያካሂዳሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ጡረታ ዐቅድ ፈንዶችና መዋጮዎች

### 6. የጡረታ መዋጮ የሚከፈልበት ደመወዝ

1. የመንግሥት ሠራተኛው በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ተቀጥሮ የተለያየ ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነ የጡረታ መዋጮ መከፈል ያለበት የመንግሥት ሠራተኛው በመረጠው አንድ መስሪያ ቤት በሚከፈለው ደመወዝ ላይ ብቻ ተመስርቶ ይሆናል፡፡ በመንግሥት ሠራተኛው ከተመረጠው የመንግሥት መስሪያ ቤትና ደመወዝ ውጪ የሚፈፀም አገልግሎት እና የሚከፈል ደመወዝ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሰረት አይታሰብም ወይም አይያዝም፡፡
2. ለሠራተኛው ደመወዝ የሚከፈለው በቀን፣ በሳምንት ፣በአስራ አምስት ቀናት ወይም በተወሰነ ቁርጥ (piece of work) ሥራ ላይ የተመሠረተ ከሆነ የጡረታ መዋጮ የሚከፈለው የወሩን ክፍያ በማዳመር ከተከፈለው ጠቅላላ ደመወዝ ላይ ይሆናል፡፡
3. የጡረታ አዋጅ 907/2007 ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያለ ሠራተኛ ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም በፊት በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ለሰጠው አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ገቢ ለማድረግ ሲጠየቅ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ሠራተኛው የነበረውን ደመወዝ መሰረት በማድረግ የሠራተኛው እና የአሠሪውን ድርሻ ጨምሮ 18% የጡረታ መዋጮ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

4. የተጠራቀመ ፕሮቪደንት ፈንድ ያለው የግል ድርጅት ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ከተዛወረና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ከጡረታ መዋጮ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መዋጮ ገቢ ከፍሎ አገልግሎቱ እንዲያዝ ከተጠየቀ ጥያቄው ሲቀርብ ሠራተኛው ያለውን ደመወዝ መሰረት በማድረግ የሠራተኛው እና የአሠሪውን ድርሻ ጨምሮ 18% እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 7. የጡረታ መዋጮ ክፍያን ስለ ማሳወቅ

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

1. የራሱንና የመንግሥት ሠራተኞቹን ድርሻ የጡረታ መዋጮ መጠን፣
2. በወሩ ውስጥ የተከፈለውን ጠቅላላ የጡረታ መዋጮ መጠን፣
3. በወሩ ውስጥ ለመንግሥት ሠራተኞች የተከፈለውን ደመወዝ፣ የክፍያውን ወርና ዓመተ ምህረት በመለየትና
4. የወሩ የጡረታ መዋጮ ገቢ ካለፈው ወር ገቢ ከተደረገው የጡረታ መዋጮ ልዩነት ያለው ከሆነ የልዩነቱን ምክንያት በመግለጽ፣

ክፍያው ከተፈፀመበት ወር ጀምሮ እስከ ሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ድረስ ማስረጃውን ለአስተዳደሩ ወይም በአስተዳደሩ ለተወከሉ ገቢ ሰብሳቢ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 8. የጡረታ መዋጮ ክፍያ ማስረጃዎችን አደራጅቶ ስለመያዝ

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሠራተኞቹን ስም ዝርዝር፣ በየወሩ የተከፈላቸውን ደመወዝና የጡረታ መዋጮ ማስረጃ አደራጅቶ የመያዝና በአስተዳደሩ ወይም አስተዳደሩ በሚወክላቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት ሲጠየቅ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
2. ገቢ ሰብሳቢ አካላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች የጡረታ መዋጮ

ገቢ ካደረጉ ከሰባት ተከታታይ ቀናት በኋላ ለአስተዳደሩ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

3. አስተዳደሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተላለፈለት ማስረጃ መሰረት የሚፈለገው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረጉን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፡፡

## ክፍል አራት

## የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች

### 9. ስለ ማስረጃዎች አቀራረብ

1. የጡረታ አበል የሚወሰነው በአዋጁ ክፍል ሁለት አንቀጽ 4፣ ክፍል 10 አንቀፅ 53 እና በዚህ መመሪያ መሰረት በሚቀርብ ማስረጃ ነው፡፡
2. ማስረጃዎቹ የሚቀርቡት አስተዳደሩ በሚያወጣቸው ቅጾችና እንደ ሁኔታው ማስረጃውን የሚሰጠው አካል በሚጠቀምበት አሰራር መሰረት ነው፡፡
3. ለጡረታ አበል አወሳሰን የሚያስፈልጉ ማሥረጃዎች ለአስተዳደሩ ወይም ለአሠሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በአድራሻ ያልተጻፈ "ለሚመለከተው ሁሉ" በሚል አድራሻ የቀረበ ከሆነ፣ ማሥረጃውን የጻፈው አሠሪ መሥሪያ ቤት በሥራ ላይ ካለ ይህንኑ ማሥረጃ ስለ ትክክለኛነቱ በደጋፊ ሰነዶች ፣ፔሮል ወይም ሌሎች ማሥረጃዎች አረጋግጦ እንዲልክ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም አሠሪ መሥሪያ ቤቱ ከሌለ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ማስተናገድ ይቻላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ማሥረጃዎች በጦርነት ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ተቋሙ በመውደሙ ማሥረጃዎቹን ማቅረብ የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ስለመውደሙ ከሚመለከተው

የመንግሥት አካል ተረጋግጦ ሲቀርብ፣ ተቋሙ በመውደሙ ምክንያት በአሠሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ማሥረጃዎቹ መገኘት ባይችሉም፣ ማሥረጃዎቹ መ/ቤቱ ተጠሪ ከሆነለት ወይም ከመ/ቤቱ የበላይ አካል ተጣርቶ ሲቀርብ አገልግሎቱ የሚያዝለት ይሆናል::

5. የአዋጁ አንቀፅ 16 ንኡስ አንቀፅ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ተደራጅተው ያልተያዙ መረጃና ማሥረጃዎችን በተመለከተ የአበል ውሳኔውን የሚሰጠው አካል በቀጥታ ለውሳኔ የሚያስፈልገውን ማሥረጃ ከአሰሪ መሥሪያ ቤቱ እንዲቀርብለት በማድረግና በማደራጀት ይሆናል፡፡

## 10 . ለዘለቄታ የጡረታ አበል ጥያቄ መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

### 1. ዕድሜ በመድረሱ ለሚጠየቅ የጡረታ አበል

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ለሚጠየቅ የጡረታ አበል፡

ሀ. የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ፣

ለ. በመጀመሪያ /ቅድሚያ/ ለሥራ ሲቀጠር የተሞላ የሥራ መጠየቂያ እና የህይወት ታሪክ ቅጽ፣

ሐ. የቅጥር ደብዳቤዎች፤

መ. በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተፈፀመ አገልግሎት ካለ በማስረጃ የተደገፈ ቅጥር፣ ስንብት፣ ዝውውር፣ እና ሌሎች መነሻና መድረሻው የተገለፀበት ለአስተዳደሩ ወይም በአሠሪው የመንግሥት መስሪያ ቤት አድራሻ የተፃፈ የአገልግሎት ማስረጃ፣

ሠ. ለሚመለከተው ሁሉ በሚል የሚቀርብ ማስረጃ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት ከሚቀርብ ደጋፊ ሰነድ ጋር፣ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. ***በጤና ጉድለት ምክንያት ስለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ***

*ከሥራ ጋር ባልተያያዘ የጤና ጉድለት ምክንያት የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ አንቀጽ (1) ከተገለጸው በተጨማሪ ሠራተኛው ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ መስራት የማይችል ለመሆኑ በሕክምና ቦርድ የተረጋገጠበት የምስክር ወረቀት መቅረብ ይኖርበታል፡፡*

3. ***በሥራ ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም የጤና ጉድለት ምክንያት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ***

*ለአንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ከተገለጸው በተጨማሪ፡-*

*ሀ. ሲቪል የመንግስት ሠራተኛው በሥራ ላይ አደጋ በደረሰበት በ30/ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደሩ የተገለጸበት የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ፣*

*ለ. እንደ ሁኔታው የፖሊስ ሪፖርት፣*

*ሐ. ስለደረሰው የአካል ጉዳት መጠንና ደመወዝ ለሚያስገኝ ማንኛውም ሥራ ብቁ ያለመሆኑ የተጋገጠበት በሕክምና ቦርድ የተሰጠ የምስክረ ወረቀት፣*

*መ. ጉዳት ከደረሰበት ቀን በፊት ባለው ወር የተከፈለውን የወር ደመወዝ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ፣ መቅረብ ይኖርበታል፡፡*

*ሠ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተጠቀሰው ቢኖርም ሠራተኛው በሥራ ላይ እያለ ከሥራው ጋር በተያያዘ በደረሰበት አደጋ ምክንያት በሞት መለየቱ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከተረጋገጠ የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ከ30 ቀን በኋላ ቢቀርብም ተቀባይነት ይኖረዋል፡*

4. ***በራስ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከሥራ ማቋረጥ ምክንያት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ፤***

ሀ. የመንግሥት ሠራተኛው በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከሥራ በመሰናበቱ የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ከተገለጸው በተጨማሪ ከሥራ ያቋረጠበትን ምክንያት የሚገልጽ ማሥረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ " ሀ " መሠረት በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ የመንግሥት ሠራተኛ ከ25 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ያለው ከሆነ በሕግ የተወሰነ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ የጡረታ አበል ይወሰንለታል፡፡

ሐ. በአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቢያንስ ከ10 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ ዕድሜው በሕግ የተወሰነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

መ. በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ዕድሜው በሕግ ከተወሰነው የጡረታ መውጫ በፊት (በ25 ዓመት አገልግሎት በ55 ዕድሜ) በራስ ፍቃድ የአገልግሎት የጡረታ አበል የተወሰነለት ባለመብት እንደገና በመቀጠር የፈጸመው አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተዳምሮ አበል የሚወሰንለት ዕድሜው በሕግ የተወሰነው የመጦሪያ ዕድሜ (60 ዓመት) ሲደርስ ብቻ ነው፡፡

## 5. <u>የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎችን በተመለከተ ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ ፤</u>

ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን በተመለከተ የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን (አምስት ዓመት) አገልግሎትን፣

ለ. ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ መሆኑን፣

የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 11. የአንድ ጊዜ ክፍያ ጥያቄ

### 1. የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት

ሀ. የመንግሥት ሠራተኛው ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ ለጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ወይም፣

ለ. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ ለሚያስገኝ ለማንኛውም ሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት፣

ሐ. ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ወይም ከአምስት ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ከኃላፊነት በመነሳቱ ምክንያት ዳረጎት ከተጠየቀ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለጹት ማስረጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2. የሥራ ላይ ጉዳት ዳረጎት

በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት የጉዳት ዳረጎት ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው ማስረጃ መቅረብ ያለበት ሲሆን በህክምና ቦርድ የተረጋገጠው ጉዳት መጠንም ከ10% ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ዳረጎት ስሌቱም ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዝ 47% ×60 በሠራተኛው ላይ በደረሰበት ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ይሆናል፡፡

### 3. ያለግባብ ወደ ፈንዱ የገባ ገንዘብ ተመላሽ ስለማድረግ

በአዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 27 መሰረት የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎት በማናቸውም ምክንያት ቢቋረጥ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ አይደረግም የሚለው የአዋጁ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛው ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በፈጸመው አገልግሎት ምክንያት ፣ ለጡረታ ስሌት ለማይያዝ አገልግሎት የተደረገ መዋጮ እንዲሁም ያለአግባብ የገባ ገንዘብ

የሠራተኛው ድርሻ ብቻ ታስቦ ለዋናው ባለመብት በአሰሪው በኩል ወይም ዋናው ባለመብት ሳይቀበል ከሞተ ከፍ/ቤት በሚቀርብ ማስረጃ መሠረት በአሰሪ መ/ቤት በኩል ለህጋዊ ተተኪ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 12. የተተኪዎች የጡረታ አበል ጥያቄ

### 1. የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል ጥያቄ

የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል ሲጠየቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (1) እና እንደሁኔታው በአንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (3) ከተዘረዘረው በተጨማሪ፡-

ሀ. ሟች የመንግስት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ በሕይወት እያለ ለአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ያቀረበውና ተመዝግቦ የተያዘ የጋብቻ ማስረጃ የሌለ ከሆነ የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያረጋግጥ በፍ/ቤት ወይም ከወሳኝ ኩነት የተሰጠ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል::

ለ. ጋብቻን በሚመለከት የቀረበው ማስረጃ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ሌላ ጋብቻ ስለመፈጸሙ ወይም ፍቺ ስለመኖሩ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል፡፡

ሐ. ሁለትና ከዚያ በላይ ጋብቻ ስለመፈጸሙ ማስረጃ በሚቀርብበት ጊዜ ቅጽ.ጡ.1 ላይ የተመዘገበችው ሚስት ሳትቀርብ ቀርታ ያልተመዘገበችው ሚስት የወሳኝ ኩነት ወይም የፍ/ቤት ማረጋገጫ ይዛ ስትቀርብ 25% የሚወሰንላት ሆኖ፣ የተመዘገበችው ሚስት በቀረበች ጊዜ የሚወሰንላት ይሆናል፡፡

መ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተመዝግባ የነበረችው የሟች ሚስት ስለመሞቷ ወይም ፍቺ

የፈጸሙ ስለመሆኑ ከወሳኝ ኩነት ወይም በፍ/ቤት አሳውጃ ማረጋገጫ የምታቀርብ ከሆነ 50% የሚወሰንላት ይሆናል፡፡

ሠ. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ለ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሶስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበት የጡረታ አበል የማግኘት መብቱን ያጣ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የጡረታ አበሉ የተቋረጠበት ባለመብት በሞት የተለየ ከሆነ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ ውዝፍ አበል ሳይጨምር ለወደፊት የተተኪው ጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

ረ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የተገለጸውን የጡረታ አበል ለመወሰን አስቀድሞ ተተኪ ሚስት ወይም ባል ጋብቻ መፈጸም አለመፈጸማቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2. የልጅ ጡረታ አበል ጥያቄ

የልጅ ጡረታ አበል ሲጠየቅ እንደ ሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10(1) እና 10(3) ከተገለጹት

በተጨማሪ፣

ሀ. ሟች የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ በሕይወት እያለ ለአሠሪው መሥሪያ ቤት የልጅ የልደት ምስክር ወረቀት አቅርቦ ያላስመዘገበ ከሆነ በፍርድ ቤት የተሰጠ የልጅነት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ለ. ሟች የመንግስት ሠራተኛ ወይም ጡረተኛ በሕይወት እያለ ለአሰሪው መሥሪያ ቤት ማስረጃ አቅርቦ ያስመዘገበ ከሆነ በተመዘገበው ማስረጃ መሠረት የጡረታ አበል የሚወሰንላቸው ልጆች በሕይወት ስለመኖራቸው ከሚኖሩበት ወረዳ ቀበሌ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ሐ. የፍርድ ቤት ማስረጃ ሳይቀርብ በአስተዳደሩ ምዝገባ መሠረት የጡረታ አበል ለሚወሰንላቸው ልጆች አበል የሚከፈለው ዋናው ባለመብት በሕይወት እያለ ባስመዘገበው የልጅ እናት ወይም አባት አማካይነት ይሆናል፡፡ ሆኖም በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት በተሰጠ የሞግዚትነት ማስረጃ መሠረት አበል የሚወሰን ከሆነ በፍርድ ቤት በተሾመ የሞግዚትነት ማስረጃ፣

መ. የጉዲፈቻ ልጅ ሲሆን የጉድፈቻ ውሉ ጉድፈቻ አድራጊው በህይወት እያለ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀበት ማስረጃ፣

መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 3. የወላጅ ጡረታ አበል ጥያቄ

የወላጆች ጡረታ አበል ሲጠየቅ እንደ ሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (1) እና 10 ንኡስ አንቀጽ (3) ከተገለጹት በተጨማሪ፡-

ሀ. በፍርድ ቤት የተሰጠ የወላጅነት ማረጋገጫ

ለ. የጉዱፈቻ ወላጅ ሲሆን የጉድፈቻ ውሉ የጉድፈቻ ልጅ በሕይወት እያለ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የፀደቀበት ማስረጃ፣

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና(ለ) መሠረት ለሚቀርብ የወላጅ ጡረታ አበል ጥያቄ በሚች ልጃቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚደረግ ድጋፍ /ዕርዳታ/ ይተዳደሩ የነበረ ለመሆኑ እና ወላጅ እናት ወይም አባት ልጃቸው በሞተበት /ችበት/ ጊዜ ስለነበራቸው የመተዳደሪያ ገቢ፣ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 4. ባለመብቱ መሞቱን ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ማስረጃ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና 12 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) መሠረት አስቀድሞ በተመዘገበ ማስረጃ መሠረት የጡረታ አበል ሲወሰን የመንግሥት ሠራተኛው ስለመሞቱ ከአሠሪው የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ባለመብቱ በጡረታ ከተገለለ በኋላ የሞተ ከሆነ ስለመሞቱ ከቀበሌ አስተዳደር ወይም

*ከሕክምና ተቋም ወይም የሞት ማስረጃ ለመስጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ ባለመብቱ የጠፋ ከሆነ ከፍ/ቤት የተሰጠ የመጥፋት ውሳኔ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡*

## 13. <u>የተተኪዎች የአንድ ጊዜ ክፍያ ጥያቄ</u>

1. *ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ለፈጸመና የሥራ ውሉ ሳይቋረጥ ለሞተ የመንግሥት ሠራተኛ የሚስት/ባል/እና የልጆች ዳረጎት ሲጠየቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣12 ንዑስ አንቀጽ (1) እና 12 ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጹት ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡፡*

2. *የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጡረታ ባለመብቱ ከሞተ በኋላ የተጠራቀመ ውዝፍ የጡረታ ገንዘብ ካለ በአዋጁ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀፅ /1/፣ 42 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና 43 መሰረት እየታሰበ ለተተኪዎች ይከፈላል፡፡*

3. *ሚች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የሚች ልጅ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ ህመምተኛ ዕድሜው ከ21 ዓመት በላይ ከሆነ ምንም ዓይነት የጡረታ አበል ሊከፈለው አይችልም፡፡*

4. *የተተኪዎች የአንድ ጊዜ የዳረጎት ክፍያ የሚፈጸመው ለሚስት /ለባል/ እና ወይም ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ፣ የአካል ጉደተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ከሆኑ ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ብቻ ነው፡፡*

## ክፍል አምስት

## የልደት ዘመን አያያዝ

### 14. ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝ የልደት ዘመን

1. ለጡረታ ተግባር የሚያዘው የልደት ዘመን የመንግሥት ሠራተኛው በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ ወይም አገልግሎቱ እንዲያዝ በተደረገ መሥሪያ ቤት ሲቀጠር ለመጀመሪያ ጊዜ /በቅድሚያ/ የመዘገበው የልደት ቀን፣ወርና ፣ዓ.ም ወይም ዕድሜ ነው፡፡

2. ለጡረታ ተግባር የሚያዘው ዕድሜ በቅድሚያ በተሞላ የሥራ መጠየቂያ ወይም የሕይወት ታሪክ መግለጫ ቅጽ ወይም የምዝገባ ቅጽ ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን ነው፡፡

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸው በማይኖርበት ጊዜ በመሥሪያ ቤቱ በመረጃነት የተያዘና የልደት ዘመን የተገለጸበት ከተዘጋጀበት ዘመን አኳያ ቅድሚያ ያለው ማስረጃ ተይዞ ይሠራል፡፡

4. የተመዘገበው የልደት ዘመን ስርዝ ድልዝ ያለው ከሆነ ማስረጃውን ውድቅ በማድረግ በተከታታይ ከተሞሉ ማስረጃዎች ቅድሚያ ያለው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ይሁንና በተከታታይ የተሞሉ ማስረጃዎችን ለመቀበል አጠራጣሪ ሁኔታ ሲፈጠር በቅድሚያ ስርዝ ድልዝ ሆኖ የተሞላውን የልደት ዘመን በፎሬንሲክ የአሻራ ምርመራ ውጤት መጀመሪያ ተመዘገበ ተብሎ የተገለጸው የልደት ዘመን ሊያዝ ይችላል፡

### 15. የልደት ቀን ፣ወርና ዓ.ም ስለ መዘገበ ሠራተኛ

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የተወለደበት ቀን፣ ወርና ፣ዓ.ም ተመዝግቦ ከተገኘ ይኸው የልደት ዘመን ተይዞ ይሰራል፡፡

## 16. የልደት ዘመን ብቻ ስለመዘገበ ሠራተኛ

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ፡-

1. ቀንና ወር ሳይጠቅስ የልደት ዘመን ብቻ መዝግቦ ከተገኘ በመሥሪያ ቤቱ በተያዘና በተከታታይ ከተመዘገቡት ዘመኑ የተለየ ቢሆንም ቅድሚያ ባለው የልደት ዘመን በተገለፀበት ማስረጃ ላይ የተመዘገበ ቀንና ወር ይያዛል፡፡ ወርና ቀን ያልተጠቀሰ ከሆነ በተመዘገበው ልደት ዘመን በጡረታ አዋጅ የተወሰነውን የመጦሪያ ዕድሜ በመደመር በሚገኘው ዘመን መጨረሻ ወር እንደሁኔታው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሆነ ነሐሴ 30 ቀን ወይም እ.ኤ.አ. ከሆነ ታህሳስ 30 ቀን ዕድሜው ለመጦሪያ እንደደረሰ ተቆጥሮ ከሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ወር አንስቶ በጡረታ ይገለላል፡፡

2. ወር በገባ በመጀመሪያ ቀን መወለዱ ከተመዘገበ ዕድሜው ለጡረታ የሚደርሰው ከተወለደበት ቀን በፊት ባለው ወር መጨረሻ ቀን ነው፡፡

3. ወር በገባ ከ2 እስከ 30 ባሉት ቀናት መወለዱን ወይም ወርና ዓ.ም ብቻ የመዘገበ ከሆነ በጡረታ የሚገለለው ከተወለደበት ወር ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ይሆናል፡፡

## 17. ዕድሜ ብቻ ስለመዘገበ የመንግሥት ሠራተኛ

የመንግሥት ሠራተኛው በቅድሚያ በተሞላው ቅጽ ላይ ዕድሜውን ብቻ የመዘገበ ከሆነ ቅጹ ከተሞላበት ቀን ፣ወርና ዓ.ም ላይ ዕድሜው ተቀንሶ ልደት ዘመኑ ይያዛል፡፡ በቅጹ ላይ ቀንና ወር ካልተገለጸ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይፈጸማል፡፡

## 18. የተለያየ የልደት ዘመንና ዕድሜ ስለ መዘገበ ሠራተኛ

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ቅድሚያ ባለው ማስረጃ ዕድሜና የልደት ዘመን እንዲመዘገብ በሚጋብዘው ቅጽ ላይ የተለያየ የልደት

ዘመንና ዕድሜ የመዘገበ ከሆነ በተከታታይ ከተሞላው ቅጽ ላይ በአንዱ ዓመተ ምህረቱን ወይም ዕድሜውን በመድገም ከመዘገበ ይኸው በቅድሚያ የተመዘገበው ዓመተ ምህረት ወይም ዕድሜ ይያዛል፡፡

2. በተከታታይ በተመዘገቡት የልደት ዘመን መረጃዎች ላይ በቅድሚያ ተመዝግቦ የነበረው ዕድሜ ወይም ዓ.ም ያልተደገመ ከሆነ በቅድሚያ በተመዘገበው ዘመን ላይ ወርና ቀን ተገልጾ ሲገኝ ይኸው ዘመን ይያዛል፣ በዘመኑ ላይ ቀንና ወር ያልተጠቀሰ ከሆነ ዕድሜው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

## 19. በመጀመሪያ ሲቀጠር የልደት ዘመኑን ስላልመዘገበ ሠራተኛ

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በሞላው ቅጽ ላይ የልደት ዘመኑ ያልተመዘገበ ከሆነ ወይም ቅጽ ያልሞላ ከሆነ በተከታታይ ከተሞሉት ቅጾች መካከል ቅድሚያ ባለው ቅጽ ላይ የተመዘገበው የልደት ዘመን ይያዛል፡፡ ሠራተኛው ቅጽ ያልሞላ ከሆነ በአሠሪው መሥሪያ ቤት የተያዘ የልደት ዘመን የተገለጸበት ቅድሚያ ባለው ማስረጃ ወይም ይህ በማይኖርበት ጊዜ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ ላይ የተገለጸ የልደት ዘመን ተይዞ ይሰራል፡፡

## 20. የልጆች ልደት ዘመን አያያዝ

1. ለልጆች የሚያዘው የልደት ዘመን የጡረታ ባለመብቱ በሕይወት እያለ በአስተዳደሩ ወይም በአሠሪ መስሪያ ቤቱ በተዘጋጁ ቅጾች ላይ ያስመዘገበው የልደት ዘመን ነው፡፡

2. የመንግሥት ሠራተኛው በህይወት እያለ የልጅ ዕድሜ ያላስመዘገበ ከሆነ ወይም ልጁ የተወለደው ሠራተኛው ከሞተ በኋላ ከሆነ ከወሳኝ ኩነት ወይም ከሕክምና ተቋማት ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ የሚቀርበው የልጅ ልደት ዘመን ይያዛል፡፡ ይህ ከሌለ ቅድሚያ ባለው ሌላ ማስረጃ ላይ የተመዘገበ የልደት ዘመን ይያዛል፡፡

3. በማስረጃው ላይ የልጅ ዕድሜ ብቻ ከተጠቀሰ መረጃው ከተዘጋጀበት ወይም ፍ/ቤት ካመለከቱበት ወርና ዓ.ም ላይ በማቀናነስ ይያዛል በማስረጃው ላይ ወር ካልተገለጸ በአበል መጠየቂያ ቅጽ ላይ የተመዘገበው ወር ይያዛል፡፡

## 21. ስለልደት ዘመን የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች

1. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሞላው ቅጽ ላይ መሥሪያ ቤቱ በመረጃነት ተይዞ የሚሠራበት ከሆነ የኃላፊ ፊርማ ባይኖረውም ቢኖረውም ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. የመንግሥት ሠራተኛው በአንድ ቀን በተሞሉ ቅጾች ማለት፡-
   ሀ. በሥራ መጠየቂያ፣
   ለ. በሕይወት ታሪክ ፎርም፣
   ሐ. በቅጹ ጡም 1 (በምዝገባ ቅጽ)፣ ላይ የተለያየ የልደት ዘመን መዝግቦ ከተገኘ ከ " ሀ " እስከ "ሐ" ከተገለጹት እንደ ቅደም ተከተላቸው በቅድሚያ የተመዘገበ የልደት ዘመኑ ይያዛል፡፡
3. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ በሞላው ቅድሚያ ባለው ቅጽ ወይም አስቀድሞ በአሠሪው መሥሪያ ቤት በተያዘ የልደት ማስረጃ መሰረት ወደ ጡረታ እንዲመደብ በሚደረግበት ጊዜ አስቀድሞ የታወቀውን የልደት ዘመን ለማስተባበል ሲባል የሚቀርበው ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የአገልግሎት ዘመን አያያዝ

## 22. ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝ አገልግሎት ዘመን

1. ለአንድ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ አበል ለመወሰን የሚያዘው የጡረታ መዋጮ እየተከፈለበት በመንግሥት መሥሪያ ቤት በቋሚነት ወይም በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ወይም በተወሰነ ጊዜ ወይም በተወሰነ ሥራ የተፈጸመ የአገልግሎት ዘመን ነው፡፡
2. የአንድ መንግሥት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመንግሥት ሠራተኛነት ከተቀጠረበት ወይም ከተመደበበት ወይም

ከተሾመበት ቀን አንስቶ በሙሉ ዓመት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ይሆናል፡፡

3. በማቋቋሚያ አዋጃቸው፣ ደንባቸው ወይም በሠራተኛ አስተዳደር ህጋቸው ስለ አገልግሎት ማራዘም ያልተደነገገላቸው መሥሪያ ቤቶች፣ በተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ለሠራተኞቻቸው የሚያራዝሙት የአገልግሎት ዘመን ለጡረታ ተግባር ይያዛል፡፡
4. በማቋቋሚያ አዋጃቸው፣ ደንባቸው ወይም በሠራተኛ አስተዳደር ህጋቸው ስለ አገልግሎት ማራዘም ያልተደነገገላቸው መሥሪያ ቤቶች፣ እንደአግባብነቱ በተቋሙ የቦርድ ሥራ አመራር ወይንም ተቋሙ ተጠሪ ለሆነለት ተቋም የበላይ አመራር ለተቋማት ሀላፊዎች የሚያራዝሙት አገልግሎት ዘመን ለጡረታ ተግባር ይያዛል ፡፡

23. ከመቀጠሪያ ዕድሜ በፊት ስለተፈፀመ አገልግሎት

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ ከተወሰነው የመቀጠሪያ ዕድሜ በፊት ተቀጥሮ አገልግሎት የፈፀመ ከሆነ ዕድሜው 14 ዓመት ከሞላ ጊዜ ጀምሮ የፈፀመው አገልግሎት ለጡረታ ተግባር ይታሰብለታል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ለጡረታ አበል አወሳሰን ስለሚያዝ ደመወዝ

24. ለጡረታ አበል ስሌት ስለሚያዝ ደመወዝ

1. ለአግለግሎት ጡረታ አበል ስሌት የሚያዘው የመንግሥት ሠራተኛው መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ የተከፈለው አማካይ ደመወዝ ነው፡፡ በመጨረሻ በተፈጸመ አገልግሎት መሰረት የተከፈለው ደመወዝ ሦስት ተከታታይ ዓመታት (36 ወራት) የማይሞላ ሆኖ ሲገኝ ቀሪውን ወደ ኋላ በመሄድ ቀደም ሲል አገልግሎት በሰጠባቸው ጊዜ ከተከፈለው የወር ደመወዝ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ቢኖርም መዋቅራዊ አደረጃጀትና የተጠና የደመወዝ ስኬል በሌለበት የግል ድርጅት በተቀጠረ በ3 ዓመት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በጡረታ የሚገለል

ሰራተኛ በጡረታ ከሚገለልበት ወር 3 ዓመት አስቀድሞ ባለው ወር ይከፈለው ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ በ25% የሚበልጥ ዓመታዊ አማካይ የደመወዝ ጭማሪ ያገኘ እንደሆነ በየዓመቱ እስከ 25% ያለው የደመወዝ ጭማሪ ብቻ በደመወዙ ላይ ተዳምሮ የ3 ዓመት አማካይ የወር ደመወዙ ተይዞ እንዲታሰብ ይደረጋል፡፡

3. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተወሰነ በኋላ በሥራ ላይ ቆይቶ የጡረታ አበል ከተጠየቀለት የጡረታ አበሉ የሚሰላው ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠበት ወርና ዓመት ምህርት ጀምሮ ወደ ኋላ የተከፈለውን የ36 ወራት አማካይ ደመወዝ በመያዝ ነው፡፡

4. በህመም ምክንያት በሥራ ላይ ለማይገኝ የመንግሥት ሠራተኛ የደመወዝ አከፋፈል በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራ ጋር ባልተያያዘ የጤና ጉድለት ምክንያት ከሥራ ለሚሠናበት የመንግሥት ሠራተኛ የሰላሳ ስድስት (36) ወር አማካኝ ደመወዝ የሚያዘው ሲከፈለው በነበረው ሙሉ የወር ደመወዝ መሰረት ነው፡፡ ሆኖም ግን ባልተከፈለው ደመወዝ ላይ የአሠሪና ሠራተኛ ድርሻ የጡረታ መዋጮ ታስቦ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

5. በሥራ ላይ ለደረሰ ጉዳት አበል ስሌት የሚያዘው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት የተከፈለ ደመወዝ ነው፡፡ ሆኖም ሠራተኛው በአገልግሎቱ የሚያገኘው አበል የተሻለ ሆኖ ሲገኝ አማካይ ደመወዝ በአገልግሎት አበል አወሳሰን መሰረት ይያዛል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>የጡረታ አበል ውሳኔና ክፍያ አፈጻጸም</u>

### 25. <u>የጡረታ አበል ውሳኔን ስለማሳወቅ</u>

ማንኛውም ዓይነት አበል ከተወሰነ በኋላ፦

ሀ. የጡረታ አበሉ ዓይነትና መጠን፣

ለ. አበሉ መከፈል የሚጀምርበት ጊዜና ቦታ

ለአበል ተቀባዩ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

## 26. <u>የጡረታ አበል ስለሚታገድበት/ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ/</u>

የጡረታ አበል ክፍያ የሚታገደው ወይም የሚቋረጠው

1. ባለመብቱ ከሞተበት፣
2. ዋናው ባለመብት ዜግነቱን ከቀየረ ዜግነቱን ከቀየረበት ጊዜ ጀምሮ፤
3. የልጅ ዕድሜ 18 ዓመት (አካል ጉዳተኛ ወይም አእምሮ ህመምተኛ ከሆነ 21 ዓመት) ከሞላበት ጊዜ፣
4. አበሉ የተወሰነው ያለአግባብ መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ፣ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ይቋረጣል፡፡
5. በአዋጁ አንቀጽ 41 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በትዳር አጋር ህይወት ማለፍ ምክንያት ዕድሚያቸው ባል 50 ሚስት 45 ዓመት በላይ ሆነው ሌላ ጋብቻ የፈፀሙ ተጋቢዎች የትዳር አጋራቸው ህይወት በማለፉ ተጨማሪ የጡረታ አበል ሲወሰንላቸው ከሁለቱ የጡረታ አበል የሚበልጠውን እንዲወስዱ ተደርጎ አነስተኛው የአበል ክፍያ ይቋረጣል፡፡
6. በአዋጁ አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ (2) አፈፃፀም የልደት ዘመን ለማረጋገጥ በመንግስት ሠራተኛው ወይም በጡረታ ባለመብቱ ወይም በተተኪው በተለያየ ጊዜያት በምዝገባ፣ በጡረታ አበል መጠየቂያ እና ልዩ ልዩ ቅጾች የተመዘገበን የልደት ዘመን ወይም ባለመብቱ በትምህርት ላይ በነበረ ጊዜ የተመዘገበ ልደት፣ከጋብቻ በፊት የተሰጠ የልደት፣ የቀበሌ ወይም የፍርድ ቤት እና የመሳሰሉትን ማስረጃዎች ማገናዘብና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 270/1994 ከወጣ በኋላ ዜግነቱን ቀይሮ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) መሠረት ከሚመለከታቸው አካል የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ያቀረበ የጡረታ መብቱን ሊያገኝ ይችላል፡፡

## 27. የዕዳ አከፋፈል

1. ለማንኛውም ባለመብት የጡረታ አበል ያለአግባብ የተከፈለው ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የመመለስ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ባለመብቱ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ከሆነ ዕዳው ከሚከፈለው አበል ላይ 1/3 ኛ (ሲሶ) እየተቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

2. ለባለመብቱ መከፈል ያለበት የአንድ ጊዜ ክፍያ (ውዝፍ) ካለ ለዕዳው እንዲተካ ተደርጎ ቀሪው ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም የአንድ ጊዜ ክፍያው ዕዳውን የማይሸፍን ከሆነ የአንድ ወር ክፍያ ተቀንሶ ለባለመብቱ እንዲከፈል ተደርጎ በየወሩ ከሚከፈለው አበል ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፀ (1) መሰረት እየተቀነሰ ገቢ ይደረጋል፡፡

3. ባለመብቱ በህይወት እያለ በፍርድ ቤት ክርክር ከጡረታ አበሉ ላይ ለሚስት (ለባል) ወይም ለልጅ ቀለብ እየተቀነሰ እንዲከፈል ውሳኔ ከተሰጠ ዋና ባለመብቱ በህይወት እስካለ ድረስ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን ባለመብቱ ህይወቱ ካለፈበት ወርና አመተ ምህረት ጀምሮ ይከፈል የነበረው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## በወኪል አማካይነት የጡረታ አበል ስለ መክፈል

## 28. የጡረታ አበል በውክልና ስለመከፈልበት ሁኔታ

አንድ የጡረታ ባለመብት፡-

1. በእርጅና፣
2. በህመም፣
3. ውጪ ሀገር በመሄድ፣
4. በእስራት፣
5. በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ፣

ምክንያት አበሉን ተከታትሎ ለማስወሰን ወይም ቀርቦ ለመቀበል በማይችልበት ሁኔታ ላይ ከሆነ ጉዳዩን በወኪል አማካይነት ለማስፈጸም ወይም አበሉን በወኪል አማካይነት ለመቀበል ይችላል፡፡

**29. የውክልና አፈጻጸም**

ውክልና የሚፈፀመው በአስተዳደሩ (በዋና መ/ቤት፣ በሪጅን ጽ/ቤቶች፣ በቅ/ጽ/ቤቶች፣ በመስክ ጽ/ቤቶች ወይም እንደሆኔታው በክፍያ ጣቢያዎች ይሆናል፡፡ ሆኖም፡-

1. ባለመብቱ ውክልና ለመስጠት ሥልጣን በተሰጠው አካል አማካይነት ውክልና ሰጥቶ ውጪ ሀገር ከሄደ በኋላ የውክልና ማስረጃው ሲቀርብ፣
2. ባለመብቱ ውክልና ሳይሰጥ ውጪ ሀገር ከሄደ በኋላ በሚኖርበት ሀገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ውክልና ሰጥቶ ማስረጃውን ሲያቀርብ፣
3. ባለመብቱ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ከሆነ በማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ተረጋግጦ ማስረጃው ሲቀርብ፣
4. ባለመብቱ በህክምና ተቋም ተኝቶ ህክምና እየተከታተለ ስለመሆኑ ከህክምና ተቋሙ የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ፣
5. ከአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች `ርቀው በሚገኙ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑና በጤና ጉደለት ወይም በእርጅና ምክንያት አበላቸውን በየወሩ ቀርበው ለመቀበል ላልቻሉ ባለመብቶች በሚኖሩበት አካባቢ ውክልና ለመስጠት ሥልጣን ባለው አካል የተፈፀመ የውክልና ማስረጃ ሲቀርብ፡፡

ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**30. ውክልና ለመፈ ፀም ስለሚቀርብ ማስረጃ**

1. ባለመብቱ የውክልና ጥያቄ ያቀረበው፡-

   ሀ. በጤና ጉድለት ምክንያት ከሆነ የጤና ጉድለቱን የሚገልጽ የሕክምና ማስረጃ፣

ለ. ወደ ውጪ ሀገር በመሄድ ምክንያት ከሆነ የባለመብቱ ፓስፖርትና መግቢያ ቪዛ ፎቶ ኮፒ፣

ሐ. በመታሰሩ ምክንያት ከሆነ ከማረሚያ ቤቱ የተሰጠ ማስረጃ፡፡

መ. የኢትዮጵያን ዜግነት በቀየረበት ሁኔታ ከሆነ የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጪ ሀገር ዜጋ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ ውክልና ይሰጣል፡፡

2. ባለመብቱ ውክልና ሳይሰጥ ወደ ውጪ ሀገር የሄደ ከሆነ በአለበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ ጽ/ቤት አማካይነት ውክልናው የተፈፀመበትን ማስረጃ ከታደሰ ፓስፖርት ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ ያስፈልጋል፣

3. በእርጅና ወይም ማስረጃ ሊቀርብበት በማይቻልበት የጤና ጉድለት ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አበሉን ቀርቦ ለመቀበል ለማይችል ባለመብት በሚመለከተው የሪጅን ወይም የቅ/ጽ/ቤት ሀላፊ እንደ ሁኔታው እየታየ ውክልና ይፈጸማል፡፡

## 31. የባለመብቱን በሕይወት መኖር ስለማረጋገጥ

1. በእርጅና፣በጤና ጉድለት እና በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በኃላፊዎች ውሳኔ በወኪል አማካይነት አበል እንዲከፈለው የተደረገ ባለመብት በሕይወት ስለመኖሩ በየሦስት ወሩ በአካል ከቀረበ ወይም ከሚኖርበት አካባቢ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ማስረጃ ሲያቀርብ ውክልናው ይራዘምለታል፡፡ ሆኖም በዓመት አንድ ጊዜ ባለመብቱ በአካል ቀርቦ መታየት አለበት፣ ነገር ግን ባለመብቱ በአካል መቅረብና መታየት የማይችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ የአስተዳደሩ ሰራተኞች ያለበት ቦታ ድረስ ሄደው በማረጋገጥ ወይም ከአካባቢው መስተዳድር በህይወት ስለመኖሩ ከተረጋገጠ ውክልናውን ሊያራዝሙለት ይችላሉ፡፡

2. ውጪ ሀገር የሚኖር ባለመብት በየዓመቱ ከሚኖርበት አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ወይም በሚኖርበት አገር ሕግና ደንብ መሰረት ውክልናውን አድሶ ማስረጃ ሲልክ ውክልናው ይራዘማል፡፡ ሆኖም ፓስፖርቱ የታደሰበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. ባለመብቱ በእስር ምክንያት በወኪል አማካይነት አበል የሚከፈለው ከሆነ በዓመት ሁለት ጊዜ በየ 6 ወሩ ከታሰረበት ማረሚያ ቤት በሕይወት ስለመኖሩ ማስረጃ ሲቀርብ ውክልናው ይራዘማል፡፡

4. የጡረታ ባለመብቱን በሕይወት መኖር ለማረጋገጥ ቢዘህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተጠቀሱት መሠረት በሚቀርብ ማስረጃ፣

   ሀ. ከተጠቀሰው ጊዜ አንድ ወር በፊት አስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ከደረሰ ወይም ወካይ በአካል ቀርቦ ከታየ የውክልናው ጊዜ ከሚያልቅበት ጊዜ አንስቶ እንደ ሁኔታው ለሦስት ወራት ወይም ለአንድ ዓመት፣

   ለ. የተጠቀሰው ጊዜ ከአለፈ በኋላ እንደ ውክልናው ዓይነት በሶስት በስድስት ወራት ወይም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ ከደረሰ ወይም በአካል ቀርቦ ከታየ ውዝፉ ተከፍሎ ማስረጃው ከደረሰበት ወይም ወካይ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ ክፍያው እንደ ሁኔታው ለሦስት፣ ስድስት ወራት ወይም ለአንድ ዓመት ጊዜ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## ክፍል አሥር

## ስለጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜና ውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰን

### 32. የተተኪዎች የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜ አወሳሰን

1. የሚስት ወይም የባል ወይም የወላጅ ጡረታ አበል ጥያቄ ባለመብቱ በሞተ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ ከቀረበ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ አበል ይከፈላል፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም አንድ ባለመብት በሞተ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባል ወይም ሚስት ወይም ወላጅ መብታቸውን ለማስከበር ለፍ/ቤት አመልክተው ከፍ/ቤት ሥነ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ምክንያት ጉዳዩ ከዘገየና በፍ/ቤት ውሳኔ

በተሰጠ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ለአስተዳደሩ ከቀረበ አበሉ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ይከፈላል፡፡

3. ሚስት ወይም ባል ወይም ወላጅ መብቱን ለማስከበር ባለመብቱ ከሞተ አምስት ዓመት በኋላ ለፍ/ቤት አስመልክቶ በፍ/ቤት ውሳኔ በተሰጠ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄው አስተዳደሩ ከቀረበ ለፍ/ቤት ካመለከተበት ወር አስንቶ አበል ይከፈላል::

4. በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀፅ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚስት ወይም የባል ወይም የወላጅ የጡረታ አበል ጥያቄ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ከተጠቀሱት ጊዜ ውጪ ከቀረበ ማስረጃው ለአስተዳደሩ ከቀረበበት ወር አንስቶ አበል ይከፈላል፡፡

5. ዕድሚያቸው ከ18 ( አካል ጉዳተኛ ከሆኑ ከ21 )ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች የጡረታ አበል ጥያቄ ሲቀርብ አበሉ ባለመብቱ ከሞተበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ይከፈላቸዋል፡፡

6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 35 እና አንቀጽ 36 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለመብቱ በመጥፋቱ ምክንያት ለተተኪ የጡረታ አበል የሚወሰነው ፍ/ቤት የመጥፋት ውሳኔ ከሰጠበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ ነው::

## 33. <u>በባለመብቱ ምክንያት ዘግይቶ ስለሚቀርብ ማስረጃ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለመደበኛ ባለመብቶችም ሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል ጥያቄ ለአስተዳደሩ ቀርቦ በጥያቄው መሰረት ውሳኔ ለመስጠት ባለመብቱ ከአሠሪው መ/ቤት ማስረጃ እንዲያቀርብ ተገልጾለት ባለመብቱ ጥያቄውን ለአሠሪው መ/ቤት አቅርቦ በተደጋጋሚ ቢያመለክትም በአሰሪ መ/ቤቱ ምክንያት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማስረጃውን ባለማቅረቡ አበል ሳይወሰንለት ከቆየ የአበሉ መነሻ ጊዜ በመብቱ መጠቀም ከሚገባው ወርና አመተ ምህረት ጀምሮ ይሆናል፡፡

## 34. <u>ተሻሽሎ ስለሚወሰን ጡረታ አበል ክፍያ ውሳኔ መነሻ ጊዜ</u>

1. የጡረታ አበል ሲወሰን ያልቀረበ የአገልግሎት፣የደመወዝና ሌላ ማስረጃ ዘግይቶ ሲቀርብ የጡረታ አበሉ እንደ ማስረጃው አቀራረብ እየታየ ከአንቀጽ 35 እስከ 36 በተገለጸው መሰረት ተሻሽሎ ይወሰናል፡፡

2. በጽኑ እስራት ምክንያት አገልግሎቱ ተቀንሶ የጡረታ አበል የተወሰነለት ባለመብት በአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀፅ (5) መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ አገልግሎቱ ተይዞ አበል ተሻሽሎ ይወሰንለታል፡፡

## 35. ስለውዝፍ ጡረታ አበል አወሳሰንና አከፋፈል

አንድ የጡረታ ባለመብት አበል ተወስኖለት እያለ፡-

1. እስከ አምስት ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ውዝፍ አበሉ እንዲከፈለው ከጠየቀ አበሉን መቀበል ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ
2. ከአምስት ዓመት በላይ አበሉን ሳይቀበል ቆይቶ ውዝፍ አበሉ እንዲከፈለው ጥያቄ ሲያቀርብ ካመለከተበት ወር አንስቶ ይከፈለዋል፡፡

## 36. የጡረታ አበል ክፍያ መነሻ ጊዜና የውዝፍ አበል አወሳሰን የሥልጣን ወሰን፡-

እስከ አምስት ዓመት ያለ ውዝፍ በሥራ ሂደቱ የውሳኔና ክፍያ ባለሙያ ይወሰናል፡፡ ሆኖም በፍ/ብሔር ሕግ ቁ/1793 ፊደል (ሐ) እና (መ) መሰረት እንደ መሬት መናወጥ ፣ ማዕበል፣ መቅሰፍትና ጦርነት የመሳሰሉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአምስት ዓመት በላይ ውዝፍ እና የክፍያ መነሻ ጊዜ ጥያቄ ሲቀርብ እንደ ሁኔታው በሥራ ሂደቱ ዳይሬክተር፣ በሪጅን ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ይወስናል፡፡

## 37. ስለ ይርጋ ጊዜ አፈጻጸም

1. ቀጥሎ ከተገለፀው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ የጡረታ አበል ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል፡፡

ሀ. የጡረታ አበል ጥያቄ ሳይቀርብ ወይም የጡረታ አበል ተወስኖ እያለ ባለመብቱ ሳይቀበል ከአምስት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከቆየ፣

ለ. የልጅ የጡረታ አበል ጥያቄ እድሜው 18 ዓመት ከሞላ ከአምስት ዓመት በኋላ ከቀረበ፣

ሐ. የዳረጎት አበል ጥያቄ ጥቅሙን ለማግኘት ከሚቻልበት ቀን ወርና ዓ/ም አንስቶ አምስት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከቆየ፣

2. በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት የተደነገገው የ3 ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚጠናቀቀው ከመጋቢት 09 ቀን 2014 ዓ/ም በፊት ነው፡፡ በመሆኑም አዋጁ ከወጣ በኋላ የሚቀርብ የውዝፍ ጡረታ አበል ጥያቄ 3 ዓመት ያልሞላው ከሆነ ብቻ በአምስት ዓመት ይርጋ ጊዜ መሰረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

3. የአዋጁ አንቀፅ 49 ንኡስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ፊደል (ሐ) እና (መ) መሰረት እንደ መሬት መናወጥ ማዕበል፣ መቅሰፍትና ጦርነት በመሳሰሉት ከባለመብቱ አቅም በላይና ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ያለፈ ጊዜ ለይርጋ አይታሰብም

## ክፍል አሥራ አንድ

## በጡረታ መብትና ጥቅም ላይ ስለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሣኔ አሰጣጥ

### 38. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት

1. ማንኛውም ባለመብት የጡረታ መብትና ጥቅምን በሚመለከት በአስተዳደሩ ባለሙያ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ከሆነ ቅሬታውን፡-

ሀ. ውሣኔ የተሰጠው በዋና መሥሪያ ቤት ከሆነ ለምዝገባና አበል ውሳኔ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣

ለ. በሪጅን ወይም በቅ/ጽ/ቤቶች ከሆነ ለሪጅኑ ወይም ለቅረንጫፍ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሐ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ የተጠቀሱት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም ኃላፊዎች የባለሙያውን ውሳኔ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለማፅደቅ ይችላሉ፡፡

2. ውሣኔን እንደገና ስለማየት

ጉዳዩ በታየበት ወቅት ያልታየ ማስረጃ ሲቀርብ ወይም በቂና ህጋዊ ምክንያት ሲኖር ቀደም ሲል የተሰጠ ውሳኔ እንደገና እንዲታይ ይደረጋል፡፡

## 3. ውሣኔን ስለማሳወቅ

ሀ. በቀረበው ቅሬታ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለአመልካቹ መገለፅ እና የገለጸው ሠራተኛ ስም ቀንና ፊርማ መስፈር ይኖርበታል፣

ለ. አመልካቹ ውሳኔው በጽሁፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ እንዲደርሰው ይደረጋል፣

ሐ. ቅሬታ አቅራቢው በውሣኔው የማይስማማ ከሆነ በሥራ ሂደቱ፣ በሪጅን ጽ/ቤቱ ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል ለማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን ሊገለፅለት ይገባል፡፡

መ. ባለመብቱ በምዝገባና አበል ውሳኔ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ በሪጅኑ ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲኖረው በዳይሬክቶሬት፣ በሪጅኑ ወይም በቅ/ጽ/ቤቱ በኩል አድራሻውን ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በማድረግ የይግባኝ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

ሠ. ማንኛውም ቅሬታ ወይም አቤቱታ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች ባለመብቱ በዋናው መስሪያ ቤት፣ በሪጅን ጽ/ቤቶች ወይም በቅ/ጽ/ቤቶች ውሣኔ በተሰጠ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይግባኙ ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ረ. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለ ብሎ የሚያምን ወገን ካለ ጉባኤው ውሳኔ በሰጠ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

4. ***ስለ መንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት***

1. *አስተዳደሩ ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮ፣የቢሮ ቁሳቁስ፣አበል እና አስፈላጊ ሠራተኞች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡*

2. *በይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጽ/ቤት ተመድበው የሚሰሩ ሠራተኞች በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ተጠሪነታቸው ለአስተዳደሩ የምዝገባና አበል ውሳኔ ዳይሬክቶሬት ይሆናል፡፡*

## ***ክፍል አስራ ሁለት***

## ***ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች***

### 39. ***ከሦስት ዓመት ባላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ምክንያት ተከልክሎ ስለነበረ የጡረታ አበል***

1. *የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ከመውጣቱ ከሰኔ 01 ቀን 1995 በፊት በተፈፀመ የወንጀል ጥፋት ምክንያት በፍርድ ቤት ከሦስት ዓመት ያላነሰ የፅኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት እና በመንግስት ሥራ ላይ የነበረና ከሃያ ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ፈጽሞ የጡረታ አበል የማግኘት መብት ያጣ የመንግስት ሠራተኛ፣*

2. *ከውሳኔው በፊት ሲከፈለው የነበረው የአገልግሎት፣ የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት የጡረታ አበል ክፍያ የተቋረጠበት ባለመብት፣*

3. *በዚሁ ምክንያት የተተኪ የጡረታ አበል የተቋረጠበት ባለመብት*

*ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ የዘለቄታ የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡*

**40.** *የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የመንግሥት ሠራተኛ የነበረና በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በፍ/ቤት ተረጋግጦ ከሦስት ዓመት ያላነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት የተወሰነበት ሆኖ፣*

ሀ. ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በኋላ በፈጸመው አገልግሎት ብቻ የዘለቄታ ወይም የዳረጎት አበል ተወስኖለት የነበረ የመንግሥት ሠራተኛ የቀድሞ አገልግሎቱ ተደምሮ ተይዞ የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት የሚያስችለው ከሆነ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ አበል ተሻሽሎ ይወሰንለታል፡፡

## 41. ከሦስት ዓመት ባለነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት የተከለከለ የዘለቄታ ጡረታ አበል ክፍያ ለማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ

1. በመንግሥት ሥራ ላይ እያለ ወይም ከሥራ የተሰናበተ ሆኖ ከሃያ ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በተወሰነበት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ምክንያት የጡረታ መብቱን ያጣ የመንግሥት ሠራተኛ ፣

**ሀ.** ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግሥት ሥራ የፈጸመውን አገልግሎት መነሻና መድረሻ የሚገልጽ በሚመለከተው የመንግሥት የሥራ ኃላፊ የተፈረመ የጽሑፍ ማስረጃ፣

**ለ.** ባለጉዳዩ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት የፈጸመ ከሆነ ከየመሥሪያ ቤቶቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸውን የጽሑፍ ማስረጃዎች፣

**ሐ.** በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ለአገልግሎት ጡረታ አበል የሚቀርቡ ማስረጃዎችን፣

**መ.** ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ስለተወሰነበት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ማስረጃ፣

**ሠ.** በመጨረሻ አገልግሎት ከፈጸመበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የአገልግሎት መነሻና መድረሻ፣ ከሥራ ከመሰናበቱ በፊት የተከፈለ የ36 ወራት ደመወዝ የተሞላበት፣ የመሥሪያ ቤቱ ማህተም የተደረገበት በኃላፊና በባለመብቱ የተፈረመ የጡረታ አበል መጠየቂያ ቅጽ.ጡ 2፣ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. ከሦስት ዓመት ያላነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት ምክንያት ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የፈጸመው አገልግሎት ተቀንሶ የዳረጎት አበል የተከፈለው የመንግሥት ሠራተኛ የተቀነሰበት አገልግሎት ተደምሮ ሲታሰብ አግባብ ባለው የጡረታ አዋጅ ድንጋጌ የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት የሚያስችለው መሆኑ ከተረጋገጠ የተከፈለውን የዳረጎት አበል በአንድ ጊዜ እንዲመልስ ተደርጎ አገልግሎቱ ተደምሮ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም አንስቶ የዘለቄታ የጡረታ አበል ይወሰንለታል፡፡

3. በፈጸመው የወንጀል ጥፋት ምክንያት በፍ/ቤት ከሦስት ዓመት ያላነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት ተወስኖበት የጡረታ መብቱን ያጣ የመንግሥት ሠራተኛ ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ የፈጸመው አገልግሎት ተደምሮ ሲታሰብ ከሃያ ዓመት ያነሰና አግባብ ባለው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት የዘለቄታ የጡረታ አበል ለማግኘት የማያስችለው ከሆነ ለመንግሥት ሠራተኛ ወይም ለተተኪዎቹ የሚከፈል የዳረጎት አበል ወይም የመዋጮ ተመላሽ አይኖርም፡፡

4. በፈጸመው የወንጀል ድርጊት በፍ/ቤት ጥፋተኛ መሆኑ ተረጋግጦ ከሦስት ዓመት ያላነሰ የጽኑ እስራት ቅጣት ስለተወሰነበት ሲከፈል የነበረው የጡረታ አበል የቀረበት (የተቋረጠበት) ባለመብት (ተተኪን ይጨምራል) ከሆነ፣

   ሀ. የጡረታ አበል ሲቀበልበት የነበረ መታወቂያ እና የክፍያ መቆጣጠሪያ በእጁ ካለ፣

   ለ. የጡረታ አበል እንዲከፈለው ከመጠየቂያ ማመልከቻ ጋር በቅርብ ጊዜ ከተነሱት 4X3 ፎቶግራፍ፣

   ሐ. በማመልከቻው ላይ የጡረታ መለያ ቁጥርና የጡረታ አበሉን ለመቀበል የሚፈልጉበትን የክፍያ አድራሻ በመጥቀስ፣

   መ. ተተኪ ከሆኑ አግባብ ባለው ፍ/ቤት የተሰጠውን የተተኪነት ማስረጃ፣

በመያዝና በአካል በመቅረብ ለአስተዳደሩ ዋና መ/ቤት ወይም ለሚቀርባቸው የአስተዳደሩ ሪጅን ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በመቅረብ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

5. የአገልግሎት፣ የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ዘለቄታ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ እያለ ወይም አገልግሎቱ ለዘለቄታ ጡረታ አበል ብቁ የሚያደርገው የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እሥራት ቅጣት ስለተወሰነበት የጡረታ መብት ያልተሰጠው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 907/2007 ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ባለመብት ተተኪዎች አዋጁ ከፀደቀበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ/ም  ጀምሮ ለወደፊት የጡረታ አበል ሊወሰን ይችላል፡፡
6. በጽኑ እስራት ምክንያት የጡረታ መብታቸውን አጥተው ለቆዩ ባለመብቶችና ተተኪዎች ማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ላይ የተመለከተው ማስረጃ ሲቀርብ በቅድሚያ የሚች የአገልግሎት ዘመን ለዘለቄታ ጡረታ አበል የሚያበቃው ስለመሆኑና ስለተተኪዎቹ ማንነትና አግባብነት ተጣርቶ ተገቢው ይወሰናል ፡፡

42. <u>የወላጅ ጡረታ አበል አከፋፈል</u>

1. ለእያንዳንዳቸው የወር ገቢ (የጡረታ አበልን ይጨምራል) እስከ ብር 2000.00 (ሁለት ሺህ ብር) የሚያገኙ ወላጆች ሟች ልጃቸው በሕይወት በነበረ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚያደርግላቸው ድጋፍ ይተዳደሩ የነበረ ለመሆኑ በአሠሪ መሥሪያ ቤት፣ በፍ/ቤት በወረዳ ወይም በቀበሌ አስተዳደር ተረጋግጦ ከቀረበለት ለእያንዳንዱ ወላጅ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

2. በየወሩ የሚከፈል የጡረታ አበልን ጨምሮ የእያንዳንዳቸው የወር ገቢ ከብር 2000.00 (ሁለት ሺህ ብር) የበለጠ ገቢ ያላቸው ወላጆች ግን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተገለፀው በተጨማሪ ተቆራጭ ገንዘቡን ከተቀበሉበት መሥሪያ ቤት ወይም ከባንክ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚቀርበው ማስረጃ ወላጆች በየወሩ በተከታታይ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሆነ ድጋፍ ሲደረግላቸው የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 43. ስለ ጡረተኞች ቆጠራ

የጡረተኞችን ብዛትና የሚከፈለውን የአበል መጠን ለማወቅ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ይካሄዳል፡፡ አፈጻጸሙ አስተዳደሩ በሚያወጣው ዝርዝር አፈፃፀም ይወሰናል፡፡

## 44. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ መመሪያ እንዲታይ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለተፈጠሩ ሕጋዊ ጉዳዮች ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 45. ስለተሻሩ መመሪያዎችና አሰራሮች

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን አሰራር ወይም ልምድ በዚህ መመሪያ በተገለጹ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 46. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በዌብ ሳይት ላይ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ዳባ ኦርያ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ